# ለሄፓታይተስ ቢ መከተብ አለብዎት?



- ሄፓታይተስ ቢ ጉበትን የሚጎዳ እና የጉበት ካንሰር ሊያስከትል የሚችል ቫይረስ ነው።
- ብዙ ሰዎች በቫይረሱ ተጠቅተው ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ህመም አይሰማቸውም ወይም የታመሙ አይመስሉም፣ ነገር ግን ቫይረሱን ለሌሎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።
- ሄፓታይተስ ቢ ን ሊከላከል የሚችል ደህንነቱን የጠበቀ እና ውጤታማ ክትባት አለ።

## ሄፓታይተስ ቢ የሚተላለፈው፡-

- በወሊድ ወቅት ከነፍሰ ጡር ሴት ወደ ልጅ
- ጾታዊ ግንኙነት
- ከታመመ ሰው ጋር በደም ንክኪ
- ምላጭ፣ የጥርስ ቡርሽ፣ ወይም የጥፍር መቁረጫን በመጋራት

## ሄፓታይተስ ቢ በሚከተሉት ነገሮች አይተላለፍም፡-

- ምግብን ወይም የመመገቢያ እቃዎችን በመጋራት
- በመተቃቀፍ፣ በመሳሳም ወይም እጅ ለእጅ በመያያዝ

# መመርመር ያለበት ማን ነው?

- ነፍሰ ጡር የሆኑ ሴቶች
- ሄፓታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር የሚኖሩ ሰዎች
- ሄፓታይተስ ቢ በብዛት በተለመደባቸው ቦታዎች፣ እንደ አፍሪካ ወይም እስያ፣ የተወለዱ፣ ወይም ቤተሰቦቻቸው በእነዚህ አካባቢዎች የተወለዱ ሰዎች
- የተወሰነ ተጋላጭነት ያላቸው ሰዎች

ለበለጠ መረጃ፡-

**www.cdc.gov/hepatitis/hbv/**
**doh.wa.gov/hepbhub**

Hep B Hub
doh.wa.gov/hepbhub

Washington State Department of Health DOH 420-408 May 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት እክል ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎ 711 (Washington Relay) ላይ ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ያድርጉ።

በ Minnesota Department of Health (የሚኒሶታ ጤና መምሪያ) ፈቃድ የተዘጋጀ